# በግሪክ ሀገር ውስጥ አለም አቀፍ ጥበቃ ለሚጠይቁ አመልካቾች ጠቃሚ እና መሰረታዊ መረጃዎች

አለም አቀፍ ጥበቃ ወይም ከለላ የሚጠይቀው ሰው ዜግነት የሌለው ወይም የውጭ ዜጋ ሲሆን ጥያቄውን በጽሁፍ ወይም በቃል በማንኛውም የግሪክ ባለስልጣን መ/ቤት አለም አቀፍ ጥበቃ መጠየቅ ይችላል።

ጥያቄውም ወደ ሀገሩ እንዳይመልሱት የሚፈራ ከሆነ ምክኒያቱም የዘር፣የሀይማኖት፣የዜግነት፣የተለየ የማህበር አባል ከሆነ፣የፖለቲካ ፓርቲ አባል ከሆነ በማሳወቅ በዚህ ምክንያት ለህይወቱ አስጊ እንደሆነ ወደ ትውልድ አገሩ ወይም ቀድሞ ወደ ነበረበት አገር ቢመለስ የሞት ፍርድ፣ስቅላት፣በአካሉ ላይ ጉዳት፣የሰው መዘባበቻ፣ውርዴት በአጠቃላይ ወደ ሀገሩ ቢመለስ ስቃይ ብሎም ለህይወቱ አስጊ እንደሆነና ብሄራዊ ወይም የእርስ በርስ ጦርነትም ሊያጋጥመው እንደሚችል ከተረጋገጠ ነው።

አለም አቀፍ ጥበቃ(ከለላ) አመልካች ተብሎ የሚጠራው ከሌላ የዱብሊኑን ስምምነት* በስራ ላይ ካዋሉ አገራት ወደ ግሪክ የተመለሰ የውጭ ዜጋም ጭምር ነው።

## የአለም አቀፍ ጥበቃ እና ከለላ ለመጠየቅ በግሪክ ሀገር ውስጥ የት ቦታ እና እንዴት ማመልከት ይቻላል?

- ማመልከቻ የመቀበል ስልጣን ያለው የጥገኝነት ጉዳይ መ/ቤት ወይም በቅርንጫፍ መ/ቤት ውስጥ የተዘጋጀ የጥገኝነትን ጉዳይ ብቻ የሚመለከት እራሱን የቻለ የአገልግሎት መስጫ ቢሮ ይገኛል።

### ማስጠንቀቂያ

**የጥገኝነት አገልግሎት መስጫ ቢሮ ማሳወቅ የሚፈልገው የማይቀበላቸው የማመልከቻ አይነቶች የሚከተሉት ናቸው :-**

A) ከዚህ በፊት ለአለም አቀፍ ጥገኝነት በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ጠይቀው ጉዳዩ በእንጥልጥል ላይ ያለ ከሆነ

B) ጥገኝነት ጠይቆ ቀይ ወረቀት ያለው ከሆነ

በተጨማሪ ደግሞ ማሳወቅ የምንፈልገው በማንኛውም አጋጣሚ የጣት አሻራ እንዲሰጥ ሊደረግ ይችላል። ይህ የሚደረገው ከዚህ በፊት የጥገኝነት ማመልከቻ አስገብቶ እንደነበርና ጉዳዩ በእንጥልጥል ላይ ያለ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው ።

- በእስር ላይ ወይም መቀበያ እና መመዝግቢያ ተቋም (ካምፕ) ውስጥ እያለ ጥገኝነት መጠየቅ የሚፈልግ ከሆነ በእስር ቤት ውስጥ ወይም መቀበያ እና መመዝገቢያ ተቋም (ካምፕ) ውስጥ ያሉ ባለስልጣናት ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከት የሚፈልጉ መሆኑን ለሚመለከተው የስደተኞች ጉዳይ መ/ቤት ባለስልጣን ያሰውቃሉ።
- ለአለም አቀፍ ጥበቃ የሚጠይቀው ግለሰብ እራሱ በአካል ቀርቦ ሲሆን ጉዳዩን በጽሑፍ ሆነ በቃል መግለጽ አለበት። በተጨማሪ ደግሞ በስሩ ለሚተዳደሩ የቤተሰብ አባላት ማመልከት ፍላጎታቸው ከሆነ እና ግሪክ ውስጥ አብረውት የሚኖሩ ከሆነ ጨምሮ ማመልከት ይችላል።

ከላይ የተጠቀሱት የቤተሰብዎ አባላት አብረዎት ወደ የጥገኝነት መ/ቤት መምጣት ይኖርባቸዋል፡፡

- ማመልከቻዎትን ሲያስገቡ ከመ/ቤቱ ሰራተኛ ጋር በቋንቋ ካልተግባቡ ቋንቋዎትን የሚናገር አስተርጓሚ እንዲቀርብ እና እንዲረዳዎት ይደረጋል።
- ማመልከቻዎትን ሲያስገቡ የመ/ቤቱ ሰራተኛ ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎች በሀቀኝነት መመለስ ይኖርብዎታል። ማንኛውም የተናገሩት ነገር ወይም ያቀረቡት መረጃ ሐሰት መሆኑ ከተረጋገጠ የጠየቁት የጥገኝነት ጥያቄ ውጤቱ ላይ አሉታዊ ተጸእኖ ያሳድራል።
- አመልካቹ ከ 18 አመት በታች ከሆነ እና ሃላፊነቱን የሚወስድ አዋቂ ከሌለ ባለስልጣኑ በአስቸኳይ ለሚመለከተው የአቃቢ ህግ ያሳውቃል፡፡ በአቃቢ ህግ ትእዛዝ መሰረት ደግሞ የኮሚቴ ተወካይ (እንደራሴ) እንዲኖረውና ማንኛውንም ሀላፊነት እንዲወስድና መብቱን እንዲያስከብር ያደርጋል። ይህ የሚሆነው በግሪክ ህግ መሰረት ወይም የአሰራር ደንብ ነው። ከ 15 አመት በታች ለሆኑ ለአለም አቀፍ ጥገኝነት ማመልከት የሚችለው ወኪሉ(እንደ ራሴው) ነው። ከ 15 አመት በላይ ከሆነ ግን ማመልከቻውን እራሱ ማስገባት ይችላል። የሚመለከተው አካል ባለስልጣን ልጁ እንክብካቤ እንዲሁም ለልጆች የተዘጋጀ የመኖሪያ ቦታ እንዲኖረው ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡
- ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ በሚያሰገቡበት ጊዜ እራሱ አመልካቹም ሆነ ከ 14 አመት በላይ የሆነ የቤተሰብ አባል ፎቶ መነሳት እና የጣት አሻራ መስጠት አለበት። የጣት አሻራውም (EURODAC) በአውሮፓ ህብረት የአሻራ መሰብሰቢያ እንዲሰፍር ይደረጋል፡፡ ምክኒያቱም የዱብሊን ሶስት (III) ስምምነት በፈጸሙ ሌሎች የአውሮፓ ሀገሮች ውስጥ ከዚህ በፊት ጥገኝነት ጠይቀው እንደነበር ለማረጋገጥ እና ጠይቀው ከነበረ በስምምነቱ መሰረት ጉዳዩ ወደዛ እንዲተላለፍ ለማድረግ ነው።
- አመልካቹ ዜግነቱን የሚያረጋግጥ ፓስፖርት ወይም ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያለው እንዲሁም ማንነቱን የሚያረጋግጥ ማንኛውንም ሰነድ ማስረከብ አለበት። ይህም የቤተሰቦትን እና የርሶን ማንነት፣ የትውልድ አገሮትን፣ከየት አገር እንደመጡ እና የቤተሰብ ፋይል ያካትታል፡፡
- በእቃው ላይም ሆነ በሰውነት አካሉ ላይ ፍተሻ ሊደረግ ይችላል፡፡ በተጨማሪም አስፈላጊ ከሆነ የህክምና ምርመራ ሊደረግ ይችላል።
- ለኢንተርቪው ወይም ለቃለ መጠይቅ ቀጠሮ የሚሰጠው የስደተኛ ጉዳይ ቢሮ ሲሆን ለአለም አቀፍ ጥገኝነት ካመለከተ በኋላ ለአመልካቾች የሚሰጥ ወረቀት ይሰጣል። ይህም ወረቀት እስከ (6) ስድስት ወር ሊያገለግል ይችላል፡፡ ይህ ወረቀት ምን ጊዜም ቢሆን ከእጁዎት መለየት የለበትም ፡፡
- ለአለም አቀፍ ጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻ በሚያስገባበት ጊዜ የሚመለከተው አካል አመልካቹ ስለጠየቀው የለአለም አቀፍ ጥበቃ ሂደት እና ሂደቱም በምን ያህል የጊዜ ገደብ እንዳለው በተጨማሪም ስለ ማንኛውም መብቱ እና ግዴታው ማሳወቅ አለበት፡፡ የሚያሳውቀው አመልካቹ በሚረዳው ወይም በሚገባው ቋንቋ መሆን አለበት።
- አመልካቹ የአስገድዶ መደፈር፣ስቃይ (ቶርቸር) ወይም ሌላ የተለየ ስቃይ የደረሰበት ከሆነ ጉዳዩ ለሚመለከተው ባለስልጣን ባስቸኳይ ማሳውቅና እርዳታ እንዲደረግለት መጠየቅ ይኖርበታል፡፡
- በተጨማሪ ደግሞ ከተባበሩት መንግስታት (UN) የስደተኞች ጉዳይ ክፍል እንዲሁም የህግ ፣የህክምና እና የስነ ልቦና ድጋፍ ከሚያቀርብ ድርጅት ጋር እንዲያገናኙት መጠየቅ ይችላል።
- አመልካቹ የጥገኝነት ጥያቄ በሚጠይቅበት ወቅት አመልካቹ የግል ጠበቃ ወይም ሌላ አማካሪ ይዞ መቅረብ ይችላል፡፡ ይህ ጉዳይ የጥገኝነት ጉዳይ ቢሮ የማይመለከተው ሲሆን ማንኛውም

አይነት ለጠበቃም ሆነ ለአማካሪ የሚያወጣው ወጭ የሚመለከተው እራሱን አመልክቹን ብቻ ነው።

- አመልካቹ ከጠበቃ ወይም ከአማካሪው ጋር መቅረብ እንደሚፈልግ ካሳወቀ በኋላ ስለጉዳዩ ከጠበቃው ወይም ከአማካሪው ጋር ተነጋግሮ እንዲቀርብ የጊዜ ገደብ ይሰጠዋል።
- አመልካቿ ሴት ከሆነች ለቃለ ምልልሱ(ለኢንተርቪው) በምትቀርብበት ጊዜ ከተቻለ ኢንተርቪውን የምታደርጋት የመ/ቤቱ ሰራተኛ እንዲሁም አስተርጓሚዋም ሴት እንድትሆን መጠየቅ ትችላለች።
- በማንኛውም ቃለ ምልልስ (ኢንተርቪው) በሚደረግበት ጊዜ አመልካቹ ኢንተርቪው የሚያደርገውን የመ/ቤቱ ሰራተኛም ሆነ አስተርጓሚ (ጾታ)ወንድ ወይም ሴት እንዲደረግለት ፍላጎቱን መግለጽ ይችላል። ይሄንን ሲያደርግ ግን ከባድ ምክኒያት እንዳለውም ጨምሮ ማሳወቅ ይኖርበታል። የጥያቄዎትን ተቀባይነት መ/ቤቱ ይወስናል። እንዲሁም ሁኔታዎች ከተመቻቹ ፍላጎትዎን ያሟላል።
- አመልካቹ ከአስራ ስምንት አመት በታች ከሆነ በወኪሉ በኩል ስለ ኢንተርቪው ማወቅ ይችላል። ወኪሉም ኢንተርቪው በሚደረግበት ጊዜ አብሮ መገኘት ይችላል በተጨማሪ አስፈላጊ ከሆነ ባለስልጣኑ ትክክለኛ እድሜውን ለማወቅ የህክምና ምርመራ እንደሚደረግ ያሳውቃል። ይሄ የሚሆነው ወኪሉም አመልካቹም ከተስማሙ ነው።

**ለአለም አቀፍ ጥበቃ እና ከለላ ጥያቄውን መሰረዝ እና ውሳኔውን ማንሳት:-**

- ጥገኝነት ከጠየቀ በኋላ በፈለገው ጊዜ ጥያቄውን መሰረዝ ይችላል። ጥያቄውን በሚሰርዝበት ጊዜ ደግሞ ለጥገኞች ጉዳይ መ/ቤት ቢሮ ክፍል አመልካቹ እራሱ በአካል በመቅረብ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት። ካሳወቀ በኋላ መ/ቤቱ ፋይሉ እንዲዘጋ ያዛል። በመቀጠል በሀገሪቷ ላይ ለመቆየት የሚያስችል ምንም አይነት የመኖሪያ ፍቃድ ስለማይኖረው አገሪቷን ለቆ መውጣት አለበት።

- **የጥገኝነት ጉዳይ መ/ቤት የማመልከቻዎት ሂደት እንዲቀጥል እንደማይፈልጉ አድርጎ ሊወስድ( አመልካቹ በሌለበት) እና ሂደቱን እንዲያቋርጥ የሚያስችሉት ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው:-**

A) በማመልከቻው መሰረት ባለ ስልጣኑ የሚጠይቃቸውን መሰረታዊ መረጃዎች ካልሰጡ

B)ለኢንተርቪው ተጠርቶ ሳይቀርብ ከቀረ

C) መቀበያ እና መመዝግቢያ ተቋም (ካምፕ) ውስጥ እያለ ከመቀበያ እና መመዝግቢያ ተቋም (ካምፕ) ጠፍቶ ወይም ሳያሳውቅ ከወጣ

D) ከፖሊስ በእስር ፈንታ የተጣለበትን ግዴታ ካልተወጣ

E) ባለስልጣናት የሰጡትን የመኖሪያ ቤት ለሚመለከተው ክፍል ሳያሳውቅ ለቆ ከሄደ

F) የጥገኝነት ቢሮ ባለስልጣን ፍቃድ ሳይሰጠው አገር ለቆ ከሄደ

G) የመኖሪያ አድራሻ ወይም የስልክ ቁጥር ቀይሮ ሊገኝበት የሚችለውን አድራሻ ለጥገኞች ቢሮ ሳያሳውቅ ከቀረ

H) የይግባኝ መ/ቤት ባለስልጣን ጥሪ አድርጎለት ሳይቀርብ ከቀረ

I) የተሰጠውን ጊዜያዊ ካርድ ለማሳደስ ግፋ ቢል ከተቃጠለበት ቀን ቀጥሎ ባለው የስራ ቀን ካልሄደ

በነዚህ ምክኒያቶች የጥገኝነት ጉዳይ ቢሮ የጥገኝነት ጥያቄ እንደማያስፈልገው በመቁጠር ሂደቱን ሊያቋርጠው ይችላል:: አመልካቹ ወደ መ/ቤቱ በመሄድ ሂደቱ መቋረጥ ያልነበረበትን ምክኒያት በመግለጽ ሂደቱ እንዲቀጥል መጠየቅ ይችላል። መ/ቤቱም አመልካቹ ያቀረበውን ምክኒያት ተመልክቶ ውሳኔ ይሰጣል። ሆኖም መ/ቤቱ ማመልከቻዎትን ውድቅ ካደረገ ይግባኝ መጠየቅ ይችላሉ::

**ለአለም አቀፍ ጥበቃ እና ከለላ (ጥገኝነት) መጠየቅ እና ሂደቱ:-**

- መ/ቤቱ በሚሰጠው የቀጠሮ ቀን ቀርበው በጥገኝነት ጉዳይ መ/ቤት ሰራተኛ አማካኝነት ቃለ መጠይቅ (ኢንተርቪው)ያደርጋሉ። ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ እውነተኛ መልሶች እንዲሁም ትክክለኛ እና የተሟሉ ማስረጃዎች ብቻ ማቅረብ እና ማንኛውም አይነት ከጉዳይዎ ጋር ተያያዥነት ያለው ማስረጃ ሳይደብቁ ሊያሳውቁ ይገባል። ያቀረቡት ማስረጃዎች እንዲሁም የሰጣችሁት ቃል እውነተኛ ካልሆነ ውሳኔው ላይ መጥፎ ተጽእኖ ያሳድራል።
- ኢንተርቪው በሚደረግበት ወቅት የመ/ቤቱ ሰራተኛ በዋነኛነት የሚያቀርባቸው ጥያቄዎች ከማመልከቻው ጋር የተያያዙ ሲሆን ስለ ማንነትዎ የሚጠቁሙ መረጃዎች፣ወደ ግሪክ እንዴት እንደመጡ፣በምን ምክንያት ያሉበትን አገር ለቀው እንደመጡ፣ዜግነት የሌሎት ከሆነ እንዲሁም ወደ አገርዎ መመለስ የማይፈልጉበት ወይም የማይችሉበትን ምክንያት ያካትታሉ። በተጨማሪ አመልካቹ ይጠቅመኛል የሚለውን ማንኛውንም ነገር ኢንተርቪው በሚያደርግበት ጊዜ ጨምሮ መናገር ይችላል።
- አመልካቹ ኢንተርቪው በሚያደርግበት ጊዜ ከመ/ቤቱ ሰራተኛ ጋር በቋንቋ መግባባት የማይችል ከሆነ አስተርጓሚ እንዲገኝ ይደረጋል።
- አመልካቹ ኢንተርቪው በሚደረግበት ጊዜ ከጠበቃው ጋር ወይም ከሌላ አማካሪ፣የስነ ልቦና ባለሙያ ፣ ከሶሻል ወርክ ሰራተኛ ወይም ሃኪም ጋር አብሮ መቅረብ ይችላል።
- በኢንተርቪው ሰአት የተደረገው ማንኛውም ንግግር በሚስጥር ይያዛል።
- ቃለ መጠይቁ ሊቀዳ ይችላል። ቃለ መጠይቁ ካልተቀዳ ሰራተኛው ሙሉ ጥያቄና መልሱን በጽሁፍ ያሰፍራል። አመልካቹ በአስተርጓሚው እርዳታ የተጻፈውን ከአረጋገጡ እንዲሁም ስህተት ካለ እርማት እንዲደረግ ከጠየቁ በኋላ ይፈርማሉ። የቅጂውን ኮፒም ሆነ የጽሑፉን ግልባጭ አመልካቹ በፈለገበት ጊዜ ጠይቆ መውሰድ ይችላል ።
- ከቃለ ምልልሱ በኋላ የጥገኝነት መ/ቤቱ የፖለቲካ ጥገኝነት፣ድጋፋዊ ጥበቃ ባለመብትነት ይገባዋል ወይም ማመልከቻው ተቀባይነት የለውም ሲል ውሳኔ ያስተላልፋል::
- ከቃለ መጠይቁ በኋላ መ/ቤቱ ውጤቱን እንዲረከቡ የሚያሳውቀው እራሱ አመልካቹ በሰጠው አድራሻ መሰረት ሲሆን ይህም ወይ በስልክ ቁጥር፣በፖስታ፣በፋክስ ወይም በ ኢ_ሜል አድራሻ ሊሆን ይችላል።
- መ/ቤቱ ውሳኔውን የሚሰጠው አመልካቹ በሚረዳው ቋንቋ በአስተርጓሚ አማካኝነት መሆን ይኖርበታል።

**ለአለም አቀፍ ጥበቃ እና ከለላ የጠየቀው ሰው ማወቅ ያለበት ግዴታዎች:-**

ማንኛውም የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካቾች ማወቅ ያለባቸው ግዴታዎች:-

- አመልካቹ አንድ ውሳኔ እስኪሰጠው ድረስ ከግሪክ ሃገር መውጣት የለበትም
- ከግሪክ ባለስልጣናት ጋር በማንኛውም ከማመልከቻዎት ወይም ማንነትዎን ከማረጋገጥ ጋር ተያያዥነት ባሏቸው ጉዳዮች መተባበር
- አመልካቹ በአካል  የጥገኝነት  ጉዳይ መ/ቤት ተገኝቶ የተሰጠውን ጊዜያዊ ካርድ ከማለቁ ቀደም ብሎ ግፋ ቢል ካለቀበት ቀን ቀጥሎ ባለው የስራ ቀን ማሳደስ
- የጥገኝነት ጉዳይ የስራ አስፈጻሚ መ/ቤት ማንኛውንም አይነት ግንኙነት የሚያደርገው አመልካቹ ባሳወቀው የመኖሪያ አድራሻ እና የስልክ ቁጥር አማካኝነት ሲሆን በዛውም አድራሻ ማንኛውንም አስፈላጊ ነገሮች ሊልክ ይችላል። ስለሆነም የአድራሻ ለውጥ በሚኖርበት ጊዜ በአስቸኳይ ለመ/ቤቱ ማሳወቅ ግዴታ አለበት።
- አመልካቹ ማመልከቻው ለሚያልፍባቸው የተለያዩ ደረጃዎች የሚሰጠውን ቀጠሮ ወይም ቀነ ገደብ የማክበር ግዴታ አለበት።

- አመልካቹ ከመንግስት ድጋፍ የሚደረግለት ከሆነ ትክክለኛ የሆነ የገንዘብ ገቢውን ማሳወቅ አለበት።
- መቀበያ እና መመዝግቢያ ተቋም (ካምፕ) ወይም ሌላ መኖሪያ ከተሰጠው ከዚህ ጋር በተያያዘ የተጣለበትን ሃላፊነት መወጣት አለበት።

**አለም አቀፍ ጥበቃ እና ከለለ የጠየቀው አመልካች ያለው መብት:-**

በግሪክ ሀገር ውስጥ ማንኛውም የጥገኝነት ጠያቂ፦

- የጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻው በእንጥልጥል ሳለ ዲፖርት ሊደረግ (ወደ ሀገሩ ሊመለስ) አይችልም።
- አመልካቹ በማንኛውም የሀገሪቷ ክፍል መዘዋወር ይችላል። ነገር ግን በተሰጠው ወረቀት ላይ የሚዘዋወርበት ቦታ ገደብ ካለው በተፈቀደለት አካባቢ ብቻ ነው መዘዋወር የሚችለው።
- ጥገኝነት የጠየቀው ግለሰብ የመኖሪያ ቤት ከሌለው ቤት እንዲሰጠው ፣ ካምፕ ውስጥ ወይም ሌላ መጠለያ እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል።
- ጥገኝነት የጠየቀው ግለሰብ በግሪክ ህግና የመተዳደሪያ ደንብ መሰረት የመስራት መብት አለው።
- አመልካቹ እንደማንኛውም የግሪክ ዜጋ ሰራተኛ እኩል የኢንሹራንስ መብትና ግዴታ አለው።
- አመልካቹ ኢንሹራንስ ወይም የገቢ ምንጭ ከሌለው የነጻ ህክምና እና የመደሀኒት አገልግሎት የማግኘት መብት አለው።
- ልጆቹም ሆነ አመልካቹ እድሜያቸው ከ18 አመት በታች ያለ ከሆነ በነጻ የመንግስት ትምህርት ቤት የመማር መብት አላቸው።
- ሴሚናር(የቴክኒክ ትምህርት) ኮርስ በመውሰድ ይችላል።
- 67% ወይም ከዛ በላይ የአካል ጉዳት ካለበት ለአካል ጉዳተኞች የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ ከመንግስት ማግኘት ይችላል። ይህ የሚሆነው መቀበያ እና መመዝግቢያ ተቋም (ካምፕ) ወይም ሌላ የመኖሪያ ቦታ ሊገኝለት ካልተቻለ ነው።
- ጥገኝነት ጠያቂው ግለሰብ ከግሪክ ሀገር ውጭ ሌላ ሀገር መሄድ አይችልም።
- ጥገኝነት አመልካቹ  ሂደቱ ሳያልቅ ቤተሰቦቹን ከትውልድ ሀገሩ ማምጣት አይችልም።

**የጥገኝነት ጥያቄዬ ለሁለተኛ ደረጃ ይታይልኝ ብሎ ይግባኝ የመጠየቅ መብት**

  - ማመልከቻዎት ውድቅ ከተደረገ ወይም ድጋፋዊ ጥበቃ ብቻ ከተፈቀደሎት እርሶ ግን የፖለቲካ ጥገኝነት ይገባኛል ብለው ካመኑ የይግባኝ ጥያቄ ወደሚመለከተው መ/ቤት ቀርበው አቤት ማለት ይችላሉ። የይግባኝ ማመልከቻዎትን በውሳኔው ላይ የተጠቀሰው ቀነ ገደብ ሳያልፍ ለክልሉ የጥገኝነት ጉዳይ መ/ቤት ወይም ለክልሉ ቅርንጫፍ የጥገኝነት ጉዳይ ቢሮ ውሳኔውን ለሰጠው መ/ቤት ማስገባት ይኖርብዎታል።

- የይግባኝ መጠየቂያው ቀነ ገደብ የሚጀምረው ውሳኔው በተሰጠበት ማግስት ነው። ነገር ግን በተለያየ ምክንያት የውሳኔው ወረቀት ያልተሰጥዎት ከሆነ ይግባኝ መጠየቅ የሚችሉት ጊዜያዊ ካርድዎ ከተቃጠለበት ቀን ወይም ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን አንስቶ እስከ 60 ቀን ድረስ ነው።
- የይግባኝ ጥያቄያዎን የይግባኝ ኮሚቴ ይመረምረዋል። ኮሚቴው ጉዳዩን የሚመረምረው በአብዛኛው በፋይሉ መሰረት ነው። አመልካቹ እንደገና ለኢንተርቪው አይጠራም። ነገር ግን ጉዳዩ መቼ እንደገና እንደሚታይ እንዲሁም ማቅረብ የሚፈልገው ተጨማሪ ሰነዶች ወይም ማስረጃ ካሉት መቼ ለይግባኝ ኮሚቴ ይዞ በመቅረብ እና መሰየት እንዲችል ይነገረዋል።
- አመልካቹ ይግባኝ ጠይቆ(ብሎ) ውጤቱን በመጠበቅ ላይ እያለ ሂደቱን ማቋረጥ ከፈለገ ማቋረጥ የሚችል ሲሆን ይህ የሚሆነው እራሱ ባለጉዳዩ በአካል የጥገኝነት ጉዳይ ቤሮ በመቅረብ ሂደቱ እንዲቋረጥልኝ ሲል በጽሁፍ ሲያሳውቅ ነው። የጥገኝነት ጉዳይ ቢሮ አመልካቹ በጠየቀው መሰረት ጉዳዩ እንዲቋረጥ ያደርጋል። በተጨማሪ አገሪቷ ላይ መቆየት የሚያስችል ምንም አይነት የመኖሪያ ፍቃድ ስለማይኖረው አገሪቷን ለቆ መሄድ አለበት።
- የይግባኝ ኮሚቴው የይግባኝ ጥያቄዎት ሂደት እንዲቀጥል እንደማይፈልጉ አድርጎ ሊወስድ እና(አመልካቹ በሌለበት) ሂደቱን ለማቋረጥ የሚያስችሉት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

1) በማመልከቻው መሰረት ባለስልጣኑ የሚጠይቃቸውን መሰረታዊ መረጃዎች ካልሰጡ

2)መቀበያ እና መመዝግቢያ ተቋም (ካምፕ) ውስጥ እያለ ከመቀበያ እና መመዝግቢያ ተቋም (ካምፕ) ጠፍቶ ወይም ሳያሳውቅ ከወጣ

3) ከፖሊስ በእስር ፈንታ የተጣለበትን ግዴታ ካልተወጣ

4) ባለስልጣናት የሰጡትን የመኖሪያ ቦታ ለሚመለከተው ክፍል ሳያሳውቅ ለቆ ከሄደ

5) የጥገኝነት ቢሮ ባለስልጣን ፍቃድ ሳይሰጠው አገር ለቆ ከሄደ

6) የመኖሪያ አድራሻ ወይም የስልክ ቁጥር ቀይሮ ሊገኝበት የሚችለውን አድራሻ ለጥገኞች ቢሮ ሳያሳውቅ ከቀረ

7) የይግባኝ መ/ቤት ባለስልጣን ጥሪ አድርጎለት ሳይቀርብ ከቀረ

8) የተሰጠውን ጊዜያዊ ካርድ ለማሳደስ ግፋ ቢል ከተቃጠለበት ቀን ቀጥሎ ባለው የስራ ቀን ካልሄደ

- የይግባኝ ኮሚቴ አመልካቹ እንደገና ኢንተርቪው ማድረግ እንዳለበት ካመነ ኢንተርቪው የሚያደርግበት ቀን ግፋ ቢል ከአምስት የስራ ቀናት በፊት እንዲዘጋጅ ይነገረዋል። በእለቱ

አመልካቹ ጠበቃ ወይም ሌላ አማካሪ ይዞ የመቅረብ መብት አለው። ይግባኝ የጠየቀው ሰው በእለቱ ሳይገኝ ቢቀርም እንኳ የይግባኝ ኮሚቴ ጉዳዩን ይመረምራል።

- የይግባኝ ተመልካች ኮሚቴ አለማዊ ጥበቃ፣ድጋፋዊ ጥበቃ ባለመብትነት ይገባዋል ወይም ይግባኙ ተቀባይነት የለውም ሲል ውሳኔ ያስተላልፋል።
- የይግባኝ ኮሚቴው ውሳኔ የሚደርሰው ከዚህ በፊት ለጥገኝነት ጥበቃ ባመለከተበት ወቅት ውሳኔው በደረሰው ሁኔታ የኮሚቴውም ውሳኔም ይደርሰዋል።
- የይግባኝ ኮሚቴ የይግባኝ ጥያቄውን ውድቅ ካደረገው ወይም ድጋፋዊ ጥበቃ ይደረግለት የሚል ከሆነ እና ይግባኝ የጠየቀው ባለ ጉዳይ የፖለቲካ ጥገኝነት ይገባኝ ነበር ብሎ ካመነና በውሳኔው ካልተስማማ ውሳኔውን በመቃወም ወደ ሚመለከተው ፍርድ ቤት በመሄድ ውሳኔው ይሰረዝልኝ የሚል ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ ። ውሳኔውን በመጠበቅ ላይ ሳሉ ወደ አገርዎ ሊላኩ የሚችሉበት አጋጣሚ አለ።

**የአለም አቀፍ ጥበቃ እና ከለላ ጠያቄዎች እስርን በተመለከተ**
ማወቅ ያለባቸው ነገሮች :-

- ለአለም አቀፍ ጥበቃ የጠየቀ አመልካች በህገ ወጥ ወደዚህ ሀገር ስለገባ እና ህገወጥ ሆኖ ስለሚኖር ብቻ አይታሰርም።
- ለአለም አቀፍ ጥበቃ ያመለከተው ግለሰብ ወንጀል ሰርቶ በእስር ቤት ያለ ከሆነ በእስር ቤት እንዲቆይ ይደረጋል።
- ለአለም አቀፍ ጥበቃ ያመለከተው ግለሰብ በህገ ወጥ መንገድ ወደ እዚህ ሀገር ስለገባ ወይም ወደ መጣበት ሀገር እንደሚመለስ ተነግሮት በመጠበቅ ላይ እያለ ከሆነና የግሪክ ፖሊስ በሌላ አይነት ሁኔታ ሊኖሩ እንደማይችሉ ካመነ በእስር እንዲቆዩ ሊያደርጉ ይችላሉ።

በእስር የሚቆዩት:-

a)የአመልካቹን ትክክለኛ ማንነት ወይም ዜግነት እንዲረጋገጥ፤

b)ማመልከቻው የተመሰረተባቸው መረጃዎች በሌላ መንገድ ሊረጋገጡ የማይችሉ ከሆነ ፤ በተለይም ከአገሩ በድብቅ ሊለቅ የሚችል ከሆነ

c) አመልካቹ የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻውን ያስገባው ወደ አገሩ እንዲላክ የወጣን ውሳኔ ሆን ብሎ ለማዘግየት ወይም ለማገድ እንደሆነ የሚያረጋግጡ ተጨባጭ ማስረጃዎች ያሉ ከሆነ

d) አመልካቹ ለሀገር ደህንነት አደገኛ ወይም ለህብረተሰቡ አስጊ ከሆነ

e) የአውሮፓ ህብረት ደንብ ቁጥር 604/2013 በሚያመለክተው መሰረት ከአገሩ በድብቅ ወደ ሌላ ቦታ ሊዛወር የሚችል ከሆነ፤ እንዲሁም የመዘዋወሩ ሂደት ከላይ በተጠቀሰው ደንብ መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ

- በእስር ላይ ባይሆኑም እንኳ የግሪክ ፖሊስ እንዲታሰሩ ሊወስን ይችላል። ይኸውም ለሀገር ህልውና ወይም ለህብረተሰቡ አስጊና አደገኛ መሆኑ ከታመነበት ነው።
- አመልካቹ በእስር ቤት የሚቆይበት ጊዜከ45 ቀን እስከ 18 ወር ሊቆይ ይችላል። እንደታሰሩበት ምክንያት ይለያያል።
- የግሪክ ፖሊስ ስራ አስኪያጅ አመልካቹ በቁጥጥር ስር እንዲውል የመወሰን መብት ያለው ሲሆን ለምን መታሰር እንዳለበት እንደወሰነ በዝርዝር ማሳወቅ አለበት።

- አመልካቹ እንዲታሰር ከተወሰነበት በውሳኔው ላይ ያለውን ተቃውሞ በተመለከተ በፕሬዝዳንቱ ወይም በክልሉ Iኛ ፍርድ ቤት ፊት አቤት ማለት ይችላል።
- አመልካቹ በእስር ላይ ያለ ከሆነ ወይም በመቀበያ እና መመዝገቢያ ተቋም (መቀበያ እና መመዝግቢያ ተቋም (ካምፕ) ) ውስጥ እያለ ለጥገኝነት ያመለከተ ከሆነ ወረቀት የሚሰጠው ከእስር ቤት ወይም ከበመቀበያ እና መመዝገቢያ ተቋም (መቀበያ እና መመዝግቢያ ተቋም (ካምፕ) ) በሚወጣበት ቀን ነው። ጉዳዩ በእንጥልጥል እስካለ ድረስ አድራሻውን ለጥገኝነት ጉዳይ ቢሮ ክፍል በአስር( 10 )ቀን ውስጥ በአካል በመቀረብ ማሳወቅ እንዲሁም ጊዜያዊ ካርድ ያልተሰጥዎት ከሆነ መውሰድ ይኖርብዎታል።

## ለአለም አቀፍ ጥበቃ እና ከለላ ለሚጠይቁ አመልካቾች አዲስና ጠቃሚ መረጃዎች

- የጥገኝነት ጥያቄው ከጥገኞች ጉዳይ ክፍልም ሆነ ከይግባኝ ኮሚቴው ውድቅ ከተደረገ ወይም ውሳኔውን በመቃወም ይግባኝ ሳይጠይቅ ቀነ ገደቡ ካለፈ በኋላ አዲስ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች ማቅረብ ከፈለገ እንደገና በአዲስ ማመልከት ይችላል።
- አዲሱን ማመልከቻ በክልሉ የየጥገኝነት ጉዳይ መ/ቤት ወይም በቅርንጫፍ የክልሉ የጥገኝነት ቢሮ ማስገባት ይችላሉ። ውድቅ የተደረገውን የውሳኔ ወረቀት ማምጣትና አዲሶቹን ጠቃሚ መረጃዎች በጽሁፍ ማሳወቅ አለብዎት። አዲሱን ማመልከቻ ካስገቡ በኋላ ጊዜያዊ ካርድ አይሰጥም።
- የጥገኝነት ጉዳይ መ/ቤት ክፍል የቀረበውን አዲስ መረጃ እንደገና መርምሮ ለአለም አቀፍ የጥገኝነት ጥያቄ ወሳኝነት እንዳላቸውና እንደሌላቸው ይወስናል።
- መ/ቤቱ አዲስ የቀረበውን ማመልከቻ ካልተቀበለው እንደገና ውሳኔውን በመቃወም ለይግባኝ ኮሚቴ በ15 ቀን ውስጥ ይግባኝ መጠየቅ ይችላል። ቀነ ገደቡ የሚቆጠረው ውሳኔውን በተቀበሉ ማግስት ነው።
- ጊዜያዊ ካርድ የሚሰጠው አዲሱ ማመልከቻ ተቀባይነት ካገኘ ብቻ ነው። ከዚያም ሂደቱ በጥገኝነት ጉዳይ /ቤት ይቀጥላል።

ወደ የጥገኝነት **መ/ቤት** ሲገቡ የጦር መሳሪያ፣ስለታማ የሆኑ እቃዎች ወይም ሌሎች ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ፣ ሊፈነዱ የሚችሉ ወይም በቀላሉ ተቀጣጣይ የሆኑ፣ ኬሚካልነት እንዲሁም አሲድነት ያላቸው ነገሮች ይዞ መግባት ክልክል መሆኑንል ልናሳውቅ እንወዳለን።
በተጨማሪም ከትንሽ ቦርሳ ወይም ሳምሰናይት በቀር ሻንጣም ሆነ ትልቅ ቦርሳ መያዝ ክልክል ነው። የሞባይል ስልክ መጠቀም የሚቻለው ከመ/ቤቱ ውጭ ባለው ቦታ ብቻ ነው። በመጨረሻ ቪዲዮ መቅዳት እና ፎቶ መነሳት በመ/ቤቱ ውስጥም ሆነ ውጭ የተከለከለ ነው።